# COVID-19 እና የሳምባ ነቀርሳ

ኮሮና ቫይረስ (ወይም COVID-19) ወረርሺኝ ሜሪላንድ ውስጥ የሚደረገውን ሳምባነቀርሳ (ወይም TB) መከላከል/ህክምና የሚሰጠውን ትኩረት ይበልጥ አስፈላጊ እና አጣዳፊ አድርጎታል።

## COVID-19 ምንድን ነው?

- COVID-19 ከአንድ ሰው ወደ ሌላው ሰው የሚሰራጭ በቫይረስ ምክንያት የሚከሰት የመተንፈሻ አካላትን የሚያጠቃ በሽታ ነው። ቫይረሱ ከባድ የሆነን በሽታ የሚያስከትል ሲሆን በአለማችን ውስጠ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሞቶች እንዲከሰቱ አድርጓል። ለ COVID-19 የሚታወቅ መድሀኒት የለም።

## የሳምባነ ቀርሳ ወይም TB ምንድን ነው?




- TB ከባድ እና አንዳንድ ጊዜ ለሞት የሚዳርግ የመተንፈሻ አካላት በሽታ (በባክቴሪያ ምክንያት የሚፈጠር) ሲሆን አብዛኛውን ጊዜ ሳምባዎችን የሚያጠቃ ሲሆን፣ ነገር ግን የሰውነትን ሌሎች ክፍሎችም ያጠቃል።
- **ሁለት አይነት TB ዎች አሉ - ተደብቆ የሚቆይ የ TB እና ንቁ የሆነ የ TB በሽታ።**
  - ተደብቆ የተቀመጠ የ **TB መበከል ካለብዎ** ወደ ሌሎች ሰዎች አያሰራጩትም። ወደ **ንቁ የሆነ TB በሽታ ሊቀየር ይችላል።**
  - TB በሽታ ካልታከመ ወደ ሌሎች ሰዎች ሊሰራጭ ይችላል።
  - ሁለቱም የ TB አይነቶች ውጤታማ በሆነ መንገድ መታከም ይችላሉ።

### የ ጋራ ምልክቶች

- **ሁሉተም COVID-19 እና TB:**
  - **ሳል ሊያስከትሉ ይችላሉ።**
  - **የትንፋሽ ማጠር ትኩሳት**
  - **ብርድ**
- **የተበከለ ሰው ሲያስነጥስ ሲያስል ወዘተ ይተላለፋል**

### ተጨማሪ COVID-19 ምልክቶች

- ምልክቶች ከ **2-14 ባሉት ከተጋላጭነበት በኋላ ባሉት ቀናት** ሊከሰቱ ይችላሉ።
- ሌሎች ምልክቶች:
  - አዲስ የመቅመስ እና ማሽተት ችሎታን ማጣት
  - የሚከረከር ጉሮሮ እና መዘጋት/ንፍጥ ያለው አፍንጫ
  - ማቅለሽለሽ ወይም ማስመለስ
  - የጡንጫ ወይም ሰውነት ህመም
  - ተቅማጥ

### ተጨማሪ የ TB በሽታ ምልክቶች

- ምልክቶች **ከሳምንታት እስከ** አመታት ባሉ ጊዜት ሊሰቱት የሚችል ሲሆን ይህም ተደበቀ የሚኖር **TB ምልክት ካልተደረገለት ነው።**
- ሌሎች ምልክቶች:
  - በምሽት ጊዜ የሚከሰት ላብ፣ ቀጣይነት ያለው የደረት ህመም
  - ደም ወይም አክታ ማሳል
  - ማብራራት የማይቻል የሰውነት ክብደት መቀንስ ወይም ድካም

## ለ TB ስጋት ያለው ማን ነው?

- ከአሜርካ፣ ካናዳ፣ አውስትራሊያ፣ ኒውዚላንድ ወይም ደቡብ/ሰሜን አውሮፓ ውጭ **በሌላ ሀገር የኖሩ ወይም የጎበኙ** ሰዎች።
- **የተዳከመ የበሽታ መከላከል አቅም** ያላቸው (ምሳሌ HIV፣ የአካል ንቅለ ተከላ፣ ካንሰር፣ ስኳር፣ የበሽታ መከላከል አቅምን የሚያዳክም መድሀኒት መጠቀም ወዘተ)
- TB ካለበት ሰው ጋር **የቅርብ የሆነ ግንኙነት።**
- **የቤት አልባነት/እስር ቤት** ታሪክ ያለው።

## ራስዎን እና ቤተሰብዎን እንዴት መጠበቅ እንዳለብዎ

- **ከፍተኛ የ TB ስጋት ካለብዎ፣** ምን ደረጃ ላይ እንዳሉ ማወቅ እና የተደበቀም ሆነ የነቃ TB ካለብዎ ህክምና ማግኘትዎ ወሳኝ ነው።
  - **TB እያለብዎ በ COVID-19** መታመም ከባድ መወሳሰቦችን ሊያስከትል ይችላል።
  - **የ TB ህክምናዎን በቋሚነት** በጤና አገልግሎት ሰጪዎ እንደሚነገርዎ ይከታተሉ።
- የ COVID-19 ጥንቃቄዎችን ይከተሉ (ማህበራዊ መራራቅ እና የፊት ጭምብል)።
- እጅዎን በተደጋጋሚ ይታጠቡ እንዲሁም ወለሎችን ያጽዱ።
- ባልታጠበ እጅ ፊትዎን አይንኩ።
- ምልክቶች ያሉብዎ ከሆነ **የጤና እንክብካቤ አገልግሎት ሰጪዎችን** ወይም **አካበቢያዊ የጤና ክፍልዎን ያግኙ**
- ለንክኪ ክትትል ጥያቄዎች በቶሎ መልስ ይስጡ።



## የት መመርመር እንዳለብዎ/ተጨማሪ መረጃ

- **COVID-19 ምርመራ:** ለ 211 ይደውሉ ወይም https://coronavirus.maryland.gov/pages/symptoms-testing#locator ይጎብኙ።
  - **ሜሪላንድ ውስጥ ስለ COVID-19 ተጨማሪ:** https://coronavirus.maryland.gov/
- **ሜሪላንድ ውስጥ ስለ TB ተጨማሪ:**
  - https://phpa.health.maryland.gov/oidpcs/ctbcp/pages/home.aspx

---

በ Los Angeles County Department of Public Health TB Control Program (ሎስ አንጀለስ ክፍለከተማ የህዝብ ጤና TB ቁጥጥር ፕሮግራም) ፈቃድ የተወሰደ
*MDH ማእከል ለ TB ቁጥጥር እና መከላከል ኖቬምበር 2020*